# የኮሮናቫይረስ (COVID-19) በአፍንጫ-በኩል የሚደረግ ምርመራ መረጃ እና ያለ-መምረጥ ቅጽ

*የወጣው፥ ጃኗሪ 5፣ 2022*

ከታች የቀረበው መረጃ እና ከዚህ ሰነድ ጋር የተያያዘው ቅጽ በዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች እና የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች ውስጥ የኮሮናቫይረስ/COVID-19 ሁለንተናዊ ምርመራን በሚመለከት ወሳኝ መረጃን ለኮሎምቢያ ዲስትሪክት (ዲስትሪክት) ተማሪዎች እና ቤተሰቦች ለማቅረብ የታሰቡ ናቸው እና በአፍንጫ-በኩል የሚደረግ ምርመራን ያለ-መምረጥ ወይም ውድቅ የማድረግ ችሎታን ያቀርባሉ። ትምህርት ቤቶች ምራቅ-ላይ የተመሰረተ ምርመራን ሊጠቀሙ እንደሚችሉ ያስታውሱ፤ ምራቅ-ላይ የተመሰረተ ምርመራን ላለ-መምረጥ መሞላት ያለበት ለብቻ የተለየ ቅጽ አለ። ይህ ቅጽ ምራቅ-ላይ የተመሰረተ ምርመራን ላለ-መምረጥ ዓላማ ጥቅም ላይ**<u>አይውልም</u>**።

በሽታ የመቆጣጠር እና መከላከል ማእከላት (CDC) የኮሮናቫይረስ/COVID-19 ምርመራን በትምህርት ቤቶች ውስጥ ማቅረብን ይመክራል፣ በወሳኝ የማህበረሰብ ስርጭት ጊዜያት ወቅት። የ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ምርመራ ትምህርት ቤቶች የCOVID-19/ኮሮናቫይረስ ኬዞችን በፍጥነት እንዲለዩ እና የCOVID-19/ኮሮናቫይረስ ስርጭትን በትምህርት ቤት ውስጥ እንዲቀንሱ ይረዳቸዋል። ለ2021-22 የትምህርት ዓመት፣ የተማሪዎ ትምህርት ቤት የአፍንጫ ጥራጊን የሚጠቀም የምርመራ ፕሮግራም ውስጥ ይሳተፋል።

በአጠቃላይ፣ ናሙናን ለመሰብሰብ የአፍንጫ-ስዋብን/ጥራጊን የሚጠቀሙ ሁለት የምርመራ ዓይነቶች አሉ። የመጀመሪያው፣ ፈጣን የአንቲጂን ምርመራ ነው፣የኮሮናቫይረስ/COVID-19 የቫይረስ ቅንጣት ነገሮች በናሙና ውስጥ እንዳሉ ለመለየት ሂደትን የሚጠቀም ነው። ሁለተኛ፣ የፖሊሜሬስ ቼይን ሪያክሽን (PCR) ምርመራ ነው፣ የቫይረስ መኖርን ለማሳየት የቫይረስ ጄኔቲክ (ዘረ-መል) (RNA) ቅንጣት ነገሮችን የሚለይ ነው። ስለ እነዚህ ምርመራዎች የበለጠ ማወቅ ይችላሉ [እዚህ]። በሁለቱም ምርመራዎች፣ የምርመራ ውጤቶች ለተማሪ ወላጅ/ሞግዚት(ወይም በቀጥታ ለአዋቂ ተማሪ)፣ ተገቢ የትምህርት ቤት ባለስልጣን(ኖች)፣ እና DC Health (ዲሲ ሄልዝ) ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ እና በልዩ ሁኔታ ይጋራል።

የአፍንጫ ስዋብ የሚጠቀም የምርመራ ፕሮግራም ውስጥ የሚሳተፉ የዲሲ የህዝብ እና የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች የምርመራ ፕሮግራሙን የሚመለከት መረጃን ለእርስዎ እና ለተማሪዎ ለማጋራት እና ውህድን ለተገቢ ባለስልጣናት ለማጋራት ይህን ቅጽ ይጠቀማሉ። ሁሉም ምርመራ በነጻ ነው።

እነዚህ ምርመራዎች ምልክት ላለው እና ለሌለው ምርመራ ሊጠቅሙ ይችላሉ።  ምልክት የሌለው ምርመራ አንድ ሰው የኮሮናቫይረስ/COVID-19 ምልክቶች ባይኖሩበትም ኮሮናቫይረስን/COVID-19 ለመለየት ይጥራል። እንዲህ ዓይነት ምልክት አልባ የማጣርያ ምርመራ ፖዘቲቭ የሆኑ ኬዞችን በፍጥነት ለመለየት እና ለብቻ ለማውጣት፣ እና በትምህርት ቤቶች ውስጥ የኮሮናቫይረስ/COVID-19 ስርጭትን ለመረዳት በዲስትሪክቱ ትምህርት ቤቶች ውስጥ እየተደረገ ነው። እርሱም የበሽታው ስርጭትን ለማሳየት ውጤታማ ስልት ነው እና ሊከሰቱ የምችሉ ወረርሽኞችን አስቀድሞ ለመለየት ሊደግፍ ይችላል። እንዲሁም የምልክት-አልባ ምርመራ የ COVID-19 ፖዘቲቭ ኬዝ የቅርብ ግንኙነቶችን ይጨምራል። ምልክት-ያለው ምርመራ ተማሪው/ዋ በትምህርት ቤት እያለ/ች የ COVID-19 ምልክቶችን ካሳየ/ች የሚደረግ ምርመራ ነው። የእነዚህ ምርመራዎች መጠቀም የቫይረሱ ተጨማሪ ስርጭትን በመከላከል እና ትምህርት ቤቶችን ለ በ-አካል ትምህርት ክፍቶ በማቆየት ተማሪዎችን፣ ወላጆችን፣ እና ማህበረሰቡን እጅግ ይጠቅማል።

የትምህርት ቤቱ የምርመራ ፕሮግራም ሁለቱም ምልክት ያለው እና የሌለው ምርመራን፣ እንዲሁም የተለያዩ ዓይነት አፍንጫ-በኩል የሚደረጉ ምርመራዎችን፣ ፈጣን የአንቲጂን ሆነ PCR፣ ያካትታል። ሁሉም እነዚህ ምርመራዎች ደህንነት ያላቸው እና ውጤታማ ናቸው፣ እንዲሁም የትምህርት ቤት ማህበረሰቦቻችንን ከኮሮናቫይረስ/COVID-19 ስርጭት ጠብቆ ለማቆየት ጠቃሚ ናቸው።

## በምን ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ ነው የኮሮናቫይረስ/COVID-19 ምርመራ የሚደረገው?

ኮሮናቫይረስ/COVID-19 ለመለየት ምርመራ ማድረግ ሊመከር የሚችልባቸው ብዙ ሁኔታዎች አሉ። ከእነዚህ ዓይነት ሁኔታዎች አንዱ የተራዘመ የትምህርት ቤት መዘጋት ጊዜን መከተል ነው፤ ለምሳሌ፣ ከትምህርት ቤት ክረምት ወይም የፀደይ እረፍት በኋላ። ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ከመመለሳቸው በፊት ምርመራ እንዲያደርጉ ትምህርት ቤቶች ሊመክሩ ይችላሉ። ከራሳቸው ህጋዊ አማካሪ ጋር ከተማከሩ በኋላ፣ ትምህርት ቤቶች ከትምህርት ቤት እረፍት ጊዜ በኋላ ኔገቲቭ የኮሮናቫይረስ/COVID-19 ምርመራ ማረጋገጫ መጠየቅን ሊያስቡ ይችላሉ። እንዲሁም ትምህርት ቤቶች በየሳምንቱ የተማሪዎች ህዝብ ናሙና የዘፈቀደ ምልክት አልባ ምርመራን በመደበኛነት ያከናውናሉ።

የኮሮናቫይረስ/COVID-19 ምልክቶች የታዩባቸው ግለሰቦች ለቫይረሱ መመርመር አለባቸው። እነዚህ ምልክቶች ትኩሳት፣ ሳል፣ ራስ-ምታት፣ ድካም፣ የመተንፈሽ ችግር፣ እና የሽታና የጣዕም ችሎታ ማጣትን ያካትታሉ፣ ግን በእዚህ ብቻ አይገደቡም።

ምርመራዎች በተጨማሪም ምልክቶች ላልታዩባቸው ግለሰቦችም ይመከራል። እነዚህ ግለሰቦች ያልተከተቡ ግለሰቦችን ያካትታሉ ግን በተጨማሪም የቅርብ ንክኪ እንዳለው የታወቀ ግለሰብ፣ የታመመ የቤተሰብ አባል ያለው፣ ከኮሎምቢያ ዲስትሪክት፣ ሜሪላንድ፣ ወይም ቨርጂኒ ውጪ የተጓዘ፣ ሰው የተሰበሰበበት የመብላት እና የመኖር ሁኔታዎች ውስጥ የነበረ ወይም የጤና እንክብካቤ መዋቅር ውስጥ የነበረ፣ ምንም እንኳ የተከተበ ቢሆንም።

## የምርመራ ፕሮግራሞቹ ምንድን ናቸው?

- **ወደ ትምህርት ቤት መመለሻ ምርመራ፥** ይህ ምርመራ ትምህርት ቤቶች ለረጅም ጊዜ እረፍቶች ከተዘጉ በኋላ የሚደረግ ነው፣ ለምሳሌ፣ ከበዓል ቀን ወቅት እና በጃኗሪ ውስጥ የሚደረግ የትምህርት ቤት መመለስ።
- **የምልክት-የሌለው ምርመራ፥** ተማሪው የCOVID-19 ቫይረስ ምርመራ ወይም ለመላው የትምህርት ቤት ህዝብ የተሰጡ ምልክት-የሌላቸው ምርመራዎችን ለመውሰድ በየሳምንቱ እንደ ዘፈቀደ የግለሰቦች ናሙና አካል ይመረጣል/ትመረጣለች።
- **የቅርብ ንክኪ/ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ምርመራ፥** ተማሪው በትምህርት ቤት መዋቅር ውስጥ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ያለበት ግለሰብ ጋር የቅርብ ግንኙነት እንደነበረው/ራት ከተለየ/ች፣ ከተጋለጠ/ች በኋላ የCOVID-19/ኮሮናቫይረስ ምርመራ ለማግኘት ብቁ ይሆናል/ትሆናለች (በትምህርት ቤቱ ከቀረበ)።
- **የምልክት-ያለው ምርመራ፥** ተማሪው/ዋ በትምህርት ቤት ውስጥ የ COVID-19 ምልክቶችን ካሳየ/ች የ COVID-19 ምርመራ ለማድረግ ብቁ ይሆናል/ትሆናለች።

## የምርመራውን ውጤት እንዴት እና መቼ አውቃለሁ?

ፈጣን የአንቲጂን ምርመራ ውጤቶች ብዙውን ጊዜ በ15 ደቂቃዎች አካባቢ ውስጥ ይወጣሉ። የPCR ምርመራዎች በላቦራቶሪ ውስጥ ይደረጋሉ እና ለማስፈጸም ከሁለት እስከ ሶስት ቀናትን መውሰድ ይችላል።

## የተማሪየን የምርመራ ውጤት ስቀበል ምን ማድረግ አለብኝ?

የተማሪው/ዋ የምርመራ ውጤት ኔገቲቭ ከሆነ፣ ያ ማለት በዚህ ጊዜ ቫይረሱ የተማሪ ናሙና ውስጥ አልተገኘም ማለት ነው። ተማሪው/ዋ በ DC Health የሚመከሩ ጭምብል መልበስ፣ የእጅ ንጽህና መጠበቅ እና ማህበራዊ ርቀት ተግባሮችን መቀጠል አለበት/ባት። ተማሪዎ መቼ ወደ ትምህርት ቤት መመለስ እንደሚችሉ በተመለከተ ተማሪዎች ከ DC Health እና ከትምህርት ቤትዎ የሚሰጡ ሁሉም መመሪያዎችን መከተል አለባቸው፣ እና ወላጆች/አሳዳጊዎች የማንኛውም ምልክቶች ህክምናን በተመለከተ ከጤና እንክብካቤ አቅራቢያቸው ጋር መመካከር አለባቸው፣ ተማሪው/ዋ፥

- ኔገቲቭ የሆነ የምርመራ ውጤት ከነበረው።ራት ግን ምልክት ካሳየ/ች፤
- ለ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ተመርምሮ ፖዘቲቭ ከሆነ ግለሰብ ጋር የቅርብ ንክኪ ከነበረው/ራት፤
- የታመመ የቤተሰብ አባል ካለው/ካላት፤ ወይም
- ከዲሲ፣ ሜሪላንድ፣ ወይም ቨርጂኒያ ውጪ ወደ ማንኛውም ቦታ ከተጓዘ።

የተማሪው/ዋ የምርመራ ውጤቶች ፖዘቲቭ ከሆኑ፣ ያ ማለት ተማሪው/ዋ ላይ ቫይረሱ አለ እና ሊያሰራጭ/ልታሰራጭ ይችላል/ትችላለች። እባክዎ በአስቸኳይ የተማሪው/ዋን የጤና እንክብካቤ አቅራቢን ያነጋግሩ። ተማሪዎች ቤት መቆየት እና ወደ ትምህርት ቤት መመለስን በተመለከተ ለትምህርት ቤቶች የተሰጠ የ DC Health መመሪያን እና ከትምህርት ቤትዎ የሚሰጥ ማንኛውም ተጨማሪ መመሪያን መከተል አለባቸው። የምርመራ ውጤቱ ሲደርስ፣ ተማሪው/ዋ ካምፓስ-ውስጥ ካለ/ች፣ ከትምህርት ቤት እስከሚወሰዱ ድረስ፣ ወደ ለብቻ ማውጣት ቦታ ይወሰዳሉ።

## የአፍንጫ ስዋብ በመጠቀም የኮሮናቫይረስ/COVID-19 ምርመራ ከማድረግ የተነሳ መከሰት የሚችሉ ስጋቶች እና ጥቅሞች ምንድን ናቸው?

መከሰት የሚችሉ የምርመራ ስጋቶች የሚጨምሩት፥

- እንደ ማንኛውም የላቦራቶሪ ምርመራ፣ ትንሽ ያለ-መደምደም ወይም የውሸት ውጤቶች ስጋት አለ።
- የአፍንጫ ስዋብ የማይመች ሊሆን ይችላል እና በዚህ ምክንያት የሚከሰቱ ውስብስብ ችግሮች በናሙና መሰብሰቢያ ወቅት ሊከሰቱ ይችላሉ።

መገኘት የሚችሉ የምርመራ ጥቅሞች የሚያካትቱት፥

- ውጤቱ፣ ከሌላ መረጃ ጋር፣ ወላጆች፣ አሳዳጊዎች፣ ወይም ተማሪዎች የልጅ እንክብካቤን የሚመለከት በእውቀት ላይ የተመሰረተ ውሳኔ እንዲሰጡ መርዳት ይችላሉ።
- የዚህ ምርመራ ውጤቶች ወደ ቤተሰብ አባላት እና ሌሎች የሚደረግ የኮሮናቫይረስ/COVID-19 ስርጭትን ለመገደብ ሊረዱ ይችላሉ።

## ተጠያቂነት

ዲስትሪክቱ፣ ትምህርት ቤቱ፣ ሠራተኞቹ፣ እና ኤጀንቶቹ ከዲስትሪክቱ የከተማ-ደረጃ የ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ምርመራ ፕሮግራም ጋር በተያያዘ ለሚከሰቱ እርምጃዎች ወይም መተላለፎች የሲቪል ተጠያቂነት ነጻ ይሆናሉ፣ የወንጀል ድርጊቶች፣ ሆን ተብሎ የሚሰራ በደል፣ ከባድ ቸልተኝነት፣ ወይም በፍላጎት የሚፈጸም የስነ-ምግባር ጉድለት በስተቀር።

## መረጃ/ደታ እና ሪፖርት ማድረግ

ከዚህ ቅጽ እና ከምርመራዎች ውጤት የሚገኝ ደታ እንደ COVID-19 ሪፖርት ማድረጊያ መስፈርቶች አካል ይሰበሰባል እና ለተገቢ ትምህርት ቤት እና የጤና ባለስልጣናት ሊጋራ ይችላል። ተማሪው/ዋ ለ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ተመርምሮ/ራ ፖዘቲቭ ከሆነ/ች የተማሪው/ዋ ማንነት ለሌሎች አይገለጽም።

## በአፍንጫ-በኩል የሚደረግ ምርመራን አለ-መምረጥ እንዴት እችላለሁ?

በአፍንጫ-በኩል ከሚደርግ ምረመራ ለመውጣት መምረጥ ከፈለጉ፣ ለተማሪዎ (ወይም እርስዎ፣ የ18 ወይም ከዚያ በላይ እድሜ ተማሪ ከሆኑ) በሚቀጥለው ገጽ ላይ ያለውን ያለ-መምረጥ ቅጽን መሙላት እና መመለስ አለብዎት። ቅጹን ወደ ልጅዎ ትምህርት ቤት ይመልሱ። ያለ-መምረጥ ምርጫዎ ይመዘገባል እና ተማሪዎ በአፍንጫ-በኩል ለሚደረግ ምርመራ አይመረጡም ወይም ብቁ አይሆኑም። ይህ ያለ-መምረጥ ቅጽ ለ 2021-22 የትምህርት ዓመት ይሰራል፣ ግን ያለ-መምረጥ ምርጫዎችን በማንኛውም ጊዜ ማንሳት ይችላሉ። ተማሪዎ (ወይም እርስዎ፣ እድሜዎ 18 ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ተማሪ ከሆኑ) የኮሮናቫይረስ/COVID-19 ምርመራ እንድቀበል/እንድትቀበል እንደሚፈልጉ የሚገልጽ የጽሁፍ ደብዳቤን ወይም ኢሜይል ዝም ብለው ለተማሪዎ ትምህርት ቤት ይላኩ።

## ይህ ያለ-መምረጥ ቅጽ መፈረም ማለት እኔ ከዚህ በኋላ ወደ ትምህርት ቤት ከመመለስ በፊት ኔገቲቭ የሆነ የCOVID-19/ኮሮናቫይረስ ምርመራ ማድረግ ማቅረብ አይጠበቅብኝም ማለት ነው?

የዚህ ቅጽ የቅድሚያ ጥቅም በትምህርት ቤት ባለስልጣን ወይም ኤጀንት ከሚሰጥ በአፍንጫ-በኩል የሚደረግ የኮሮቫይረስ/COVID-19 ምርመራን ላለ-መምረጥ ነው። ትምህርት ቤቶች እና የአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲዎች ይህ ቅጽ ወደ ትምህርት ቤት ለመመለስ ኔገቲቭ የኮሮናቫይረስ/COVID-19 የምርመራ ምትክ ሆኖ ይቆም እንደሆነ ይወስናሉ።



osse.dc.gov @OSSEDC @osse.dc (202) 727-6436
WE ARE WASHINGTON DC GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR

## የCOVID-19/ኮሮናቫይረስ በአፍንጫ-በኩል የሚደርግ ምርመራን ያለ-መምረጥ ቅጽ

**ይህ ቅጽ ማንኛውም በትምህርት ቤቶች ውስጥ በአፍንጫ-በኩል የሚደረግ የኮሮናቫይረስ/COVID-19 ምርመራ (ፈጣን የአንቲጅን ወይም PCR)፣ ምልክት ላለውም ሆነ ለሌለው ምርመራ፣ ውድቅ ለማድረግ ወይም ከስምምነት ለመውጣት እና ላለ-መምረጥ በተለየ ሁኔታ ይጠቅማል።**

| **የመገኛ መረጃ** \| በወላጅ/አሳዳጊ/ተማሪ የሚሞላ (18 ወይም ከዚያ በላይ እድሜ ከሆነ/ች) | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **የተማሪ የአያት ስም፣** | **የተማሪ የመጠሪያ ስም፣** | | **የትውልድ ቀን፣** | |
| **የትምህርት ቤት ስም፥** | | | **ቀጠና/ዋርድ፥** | |
| **የቤት አድራሻ፥** | **አፓርታማ፥** | **ከተማ፣** | **ክልል፣** | **ዚፕ፥** |
| **የወላጅ/አሳዳጊ ስም፥** | **ስልክ ፥** | **ኢሜይል፣** | | |
| **የድንገተኛ ጊዜ ተጠሪ ስም፥** | **የድንገተኛ ጊዜ ተጠሪ ስልክ፥** | | | |

**ከታች በመፈረም ፣ እኔ ይህን እያልኩ ነው፥**

- የተሰጠው መረጃ በአፍንጫ-በኩል የሚደረግ የኮሮናቫይረስ/COVID-19 ምርመራ ጋር ስለሚገናኝ፣ የአፍንጫ በኩል የሚደረግ ምርመራ ስጋቶች እና ጥቅሞችን ጨምሮ፣ እንብቤያለሁ እናም እረዳለሁ እና በዚህ የኮሮናቫይረስ/COVID-19 ምርመራ ፕሮግራም ውስጥ ተማሪዬ (ወይም እራሴ፣ እድሜዬ 18 ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ) ለኮሮናቫይረስ/COVID-19 ኢንፌክሽን እንዲመረመር/እንድትመረመር ስምምነት መስጠትን ውድቅ አደርጋለሁ።
- ስምምነትን ውድቅ ማድረጌ በብቸኝነት እና በልዩ ሁኔታ በዚህ ውስጥ የተገለጸ በአፍንጫ-በኩል የሚደረግ ስዋብ ምርመራ ጋር የተያያዘ ነው እና በ 2021-22 የትምህርት ዓመት ለሚደረግ ለማንኛውም ምራቅ-ላይ የተመሰረተ የኮሮናቫይረስ/COVID-19 ምርመራ ወይም ማጣሪያ አይደለም።
- የእኔ ውድቅ-ማድረግ ለ 2021-22 የትምህርት ዓመት ተቀባይነት አለው፣ ስምምነቴን እንደሚሰጥ ከተማሪየ ትምህርት ቤት ለተወከለ ተጠሪ ሰው በጽሁፍ ካሳወቅኩት በስተቀር።
- ይህን ቅጽ በነጻ እና በገዛ ፈቃዴ ነው የፈረምኩት፣ እና ከላይ ለተጠቀሰ ተማሪ (ወይም ለራሴ፣ እድሜየ ከ18 ዓመት በላይ የሆነ ተማሪ ከሆንኩኝ) ውሳኔዎችን ለማሳለፍ ህጋዊ ስልጣን አለኝ።
- ኮሮናቫይረስ/COVID-19 ትኩሳት፣ ሳል፣ ራስ-ምታት፣ ድካም፣ የትንፋሽ ችግር፣ እና የሽታ እና የጣዕም ችሎታ ማጣትን የሚጨምር ምልክቶች ያሉት ተላላፊ በሽታ እንደሆነ እረዳለሁ። ቫይረሱ ሆስፒታል መግባት፣ ከባድ ህመም፣ እና ከሞትም ጋር ተሳስሯል።
- እኔ እድሜዬ 18 ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ተማሪ ከሆንኩ፣ ለእራሴ የጤና እንክብካቤ ህጋዊነት ባለው ሁኔታ መስማማት እንደሚችል፣ እና "ለእኔ ተማሪ" የሚላኩት ለእኔ እንደሚላኩ/እንደሚጠቀሱ እረዳለሁ። ይህንን ቅጽ እራሴን ወክዬ ሊፈርም እንደሚችል እረዳለሁ።

_______________________________________________

የወላጅ/አሳዳጊ የስምምነት ፊርማ (ተማሪ ከ18 ዓመት በታች ከሆነ/ች) ቀን (ወወ/ቀቀ/ዓዓዓዓ)

_______________________________________________

የተማሪ ፊርማ (እድሜው/ዋ ከ18 ዓመታት ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ) ቀን (ወወ/ቀቀ/ዓዓዓዓ)